አዋጅ ቁጥር --------2016

**የዓለማቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን አንቀጽ 50(ሀ) እና አንቀጽ 56 ለማሻሻል የቀረበውን ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ**

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል እ.ኤ.አ. በህዳር 7 ቀን 1944 ያጸደቀችው የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽንን ፈራሚ በመሆኗ፣

የኮንቬንሽኑ አንቀጽ 50 (ሀ) እና አንቀጽ 56 መሻሻል ለሀገራችን ጥቅሞች መከበርና በዓለም አቀፍ መድረኮች የሚኖራትን የውክልናና ተሰሚነት ዕድል የሚያሰፋ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ (1) እና (12) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የአለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን አንቀጽ 50(ሀ) እና አንቀጽ 56 በማሻሻል የቀረበውን ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ………/2016"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የፕሮቶኮሉ መፅደቅ**

   የዓለማቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት 39ኛው ጠቅላላ ጉባዔ እ.ኤ.አ. ጥቅምት 6 ቀን 2016 ያሳለፈው የኮንቬንሽኑ አንቀጽ 50(ሀ) እና አንቀጽ 56 ማሻሻያ ፕሮቶኮል በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

3. **የሥምምነቱ አስፈፃሚ አካል፣**

   የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ማሻሻያው በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

4. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ……………….. ቀን 2016 ዓ.ም.

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዝዳንት

# የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን አንቀጽ 50(ሀ) እና አንቀጽ 56 ማሻሻያ ፕሮቶኮሎች ማጸደቂያ ረቂቅ አዋጅ አጭር መግለጫ

## የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን አንቀጽ 50(a) እና አንቀጽ 56 ማሻሻያ ፕሮቶኮሎች ማጸደቂያ ረቂቅ አዋጅ አጭር መግለጫ

ኢትዮጵያ በአቪዬሽን ዘርፍ ቀደምት ታሪክ ካላቸውና እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 7 ቀን 1944 የጸደቀውን የዓለማቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን (የቺካጎ ኮንቬንሽን) በመፈረም የዓለማቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ካቋቋሙት የመጀመሪያዎቹ የዓለም ሀገራት አንዷ ስትሆን በዓለማቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ደረጃዎችና አሠራሮች የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው ሀገራት ተርታ የምትመደብ ሀገር ነች ፡፡

ይህም ጠንካራ የሬጉላቶሪ ተቋም ለመገንባትና የሀገራችን የአየር ትራንስፖርት ዘርፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጡ የአቪዬሽን ደህንነት (Safety) እና ሴኩሪቲ (Security) ያሚላና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ በዘርፉ ያላትን መልካም ስምና ዝና/ገጽታ ከማስጠበቁም ባለፈ ከአፍሪካ ግንባር ቀደም የሆነ ብሔራዊ አየር መንገድ እና ከፍተኛ የመንገዶኞች እንዲሁም ሸቀጦች መተላለፊያ የሆነ ኤርፖርት እንዲኖራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

የአየር ትራንስፖርት ዘርፍ ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው እንደመሆኑና በሉዓላዊ ግዛቶችና የአየር ክልሎች መካከል ጭምር የሚደረግ የበረራ አገልግሎት እንደመሆኑ መጠን አገልግሎቱም ሆነ ቁጥጥሩ በዋናነት በዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች የሚመራ ሲሆን በየጊዜው የሚሻሻሉና እንደነባራዊ ሁኔታ አዳዲስ አለም አቀፍ የህግ ማዕቀፍ የሚዘጋጅለት ዘርፍ ነው።

በአሁን ሰዓት ሀገራችን የተቀበለቸው የቺካጐ ስምምነትና ተቀጽላዎቹ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር ቀዳሚ መሠረት ሲሆን ሌሎች ዓለም አቀፍ የሕግ ሥርዓቶችና ፕሮቶኮሎች ወጥተውም ትግበራ ውስጥ ገብተዋል።

ይህ ደሞ በዋናነት የሚከናወነው ሀገራችን መስራች አባል በሆነችበት በዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት (ICAO) አማካኝነት ነዉ፡፡

የዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት (ICAO) የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት በየሶስት አመት በሚካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ የተቋሙ ከፍተኛ አስፈጻሚ አካል የሆነና 36 ሀገራት ተወካዬች ያቀፈ ቋሚ ካውንስል አለው ፡፡

እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 7 ቀን 1944 የቺካጎ ኮንቬንሽን የፈረሙ ሀገራት 52 ብቻ የነበሩ ሲሆን የአባል ሀገራት ቁጥር በየጊዜው በመጨመሩ ምክንያት የካውንስሉ አባላት እያደገ ካለው የአባል ሀገራት ቁጥጥር ጋር ለማጣጣም በማሰብ እ.ኤ.አ. በ1961፣ 1971፣ 1974 በአራት ተከታታይ ማሻሻያዎች የካውንስሉ አባላት ቁጥር ቀድሞ ከነበረው ከ21 ወደ 36 ደረጃ በደረጃ እንዲያድግ ተደርጓል።

ካውንስሉ ከሚያከናውናቸው ዘርፈ ብዙ ስራዎች መካከል አባል ሀገራት የሚተገብሯቸው ወይም ለከተሏቸው የሚገቡ የአየር ትራንስፖርትና የኤር ናቪጌሽን አገልግሎት እንዲሁም የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች ደረጃዎችና ተመራጭ ነት ያላቸው አሰራሮች ማውጣት ይገኝበታል፡፡ ካውንስሉ ኮንቬሽኑና ኮንቬሽኑን ተከትሎ የወጡትን ደረጃዎችና ተመራጭ ነት ያላቸው አሰራሮች በማይተገብሩና በሚጥሱ ሀገራት ላይ የሴፍቲ ደረጃዎችን በማውጣት ለአባል ሀገራት ያሳውቃል ለጠቅላላ ጉባኤውም የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል ፡፡

በዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት (ICAO) አማካኝነት እስካሁን ከአስራ ሁለት ሺ በላይ ደረጃዎችና ተማራጭነት ያላቸው አሰራሮች (SARPS) ተዘጋጅተው በአባል ሀገራት በመተግበር ላይ ይገኛሉ።

በመሆኑም የኢንዱስትሪው እድገትም ሆነ የቁጥጥር ውጤታማነት የሚመሰረተው በዋናነት በእነኝህ ዓለም ዓቀፍ ደንቦች፣ እና ስታንዳርዶች ትግበራ በመሆኑ በድርጅቱ ውስጥ በተደራጀና በንቃት በመሳተፍ የሚወጡ ስምምነቶች፣ ህጎችና ስታንዳርዶች የሃገራችንን ጥቅም ያስጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግና በቅርበት መከታተል አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህም መነሻ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. ከ2005-2007 እና 2008-2010 ባሉ 2 ዙሮች (terms) ለ6 ተከታታይ ዓመታት 19 አባል ሀገራትን ከሚወክለው የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ ምድብ ተወዳድራ በማሸነፍ ከፍተኛው ውሳኔ ሰጪ አካል በሆነው ካውንስል አባል በመሆን አገልግላለች፤

በተጨማሪም እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 27 ቀን እስከ ኦክቶበር 7 ቀን 2022 በካናዳ ሞንቴሪያል በተካሄደው 41ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በምድብ ሶስት በመወዳደር ከቀዳሚ ተመራጭ ሀገራት መካከል በመሆን የካውንስል አባል መሆን ችላለች፡፡

የዓለማቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 27/2016 እስከኦክቶበር 6/2016 በሞንትሪያል ካናዳ ባካሄደውና በወቅቱ ከ191ዱ አባላት 170ዎቹ የኮንቬንሽኑ ፈራሚና አባል ሀገራት በተሳተፉበት የካውንስሉ 39ኛው ጠቅላላ ጉባዔ

1) በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 50(a) የተደነገገውን 36 የካውንስል አባል ሀገራት ቁጥር ወደ40 ከፍ እንዲል፣

2) በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 56 የተደነገገውን 19 የኤር ናቪጌሽን ኮሚሽን አባል ሀገራት ቁጥር ወደ 21 ከፍ እንዲል የሚያስችል የኮንቬንሽኑ ማሻሻያ ሁለት ፕሮቶኮሎችን Resolution A39-5 እና Resolution A39-7 ያጸደቀ ሲሆን ማሻሻያዎቹንም አባል አገራት የሀገራዊ ህጋቸው አካል እንዲያደረጉት /ratify/ ምክረ ሀሳብ አስቀምጧል ፡፡

ይህም የሆነበት ምክንያቶች መካከል የድርጅቱ አባል ሀገራት ቁጥር ወደ 191 በማደጉ በካውንስሉ አባላት ምርጫ ሀገራት በቂ ውክልና እንዲኖራቸው ለማስቻል፣ ሁሉም የአለም ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች በማዳርስ ለተሻለ መልክዓ ምድራዊ ውክልና ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲሁም ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁሉም ልዩ ኤጀንሲዎች የአስፈፃሚ አካላትን አባልነት በመጨማራቸው ምክንያት ድርጅቱ (ICAO) በዚሁ መሰረት ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

ማሻሻያዎቹን እስካሁን 80 አባል ሀገራት የፈርመበትና ያጸደቁት ሲሆን ከጠቅላላ አባል ሀገራት ውስጥ 128 የሚሆኑት በየሀገሮቻቸው ሲያጸድቁት ወደ ተግባር ይገባል፡፡

እነዚህ የማሻሻያ ፕሮቶኮሎች ጸድቆ መተግበር ቀደም ሲል 54 ሀገራትን የያዘችው አፍሪካ 36 አባላት በሚወከሉበት የዓለማቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ካውንስል የተሰጣት ውክልና 8 ብቻ የነበረ በመሆኑ የካውንስል አባላቱ ቁጥር ወደ 40 ከፍ ሲል እንደ አህጉር ቢያንስ ከ1-2 ተጨማሪ ውክልና ይኖራታል ተብሎ ይጠበቃል፣ ይህም ሀገራችን ከተቀሩት የአፍሪካ ሀገራት አንጻር በዘርፉ የተሻለ ቁመና አላቸው ከሚባሉት በጣት የሚቆጠሩ ሀገራት መካከል በመሆኗ የካውንስል አባልነት ዕድል በድጋሚ እንድታገኝ ይረዳታል፣

በተመሳሳይ የኤር ናቪጌሽን ኮሚሽን አባላት ቁጥር ከ19 ወደ 21 እንዲያድግ በመደረጉም በቀጣይ የኮሚሽኑ አባል ለመሆን የሚኖራትን ዕድል የሚያሰፋ ሲሆን ዓለማቀፍ ተሰሚነትን፣የኤር ናቪጌሽን አገልግሎቱን ተለዋዋጭና የቴክኖሎጂ ሁኔታ ፈጥኖ በመረዳት ለአገልግሎቱ የበለጠ መሻሻል ዕወቀትና ክህሎት የሚገኝበት ይሆናል፤

ባጠቃላይ የኮንቬንሽኑ ማሻሻያ ፕሮቶኮሎች ማጸደቅ ሀገራችን በድርጅቱ ካውንስል ውስጥ በምድብ ሁለት ውስጥ በመወዳደር በቋሚነት አባል የመሆን እድሏን በእጅጉ ስለሚጨምረው እንዲሁም የሀገራችን የሲቪል አቪዬሽን መዋቅሯ ዓለማቀፍ እውቅና ለማጉላትና ለሀገራችን ጥቅም መከበርና በዓለም ዓቀፍ መድረኮች የሚኖራትን ተሰሚነት ዕድል ለማስፋትና በአለም አቀፍ መድረኮች ግንባር ቀደም ሆና ለመንቀሳቀስ ይረዳታል፡፡

በመሆኑም ፕሮቶኮሎቹን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ እየጠየቅን ለሀገራችን ጥቅም መከበርና በዓለም ዓቀፍ መድረኮች የሚኖራትን ውክልና እና ተሰሚነት ዕድል ከማስፋቱም ባሻገር ከፍላጎቷ በተጻራሪ የሚቆሙ ኃይሎችንም በቅርበት ለመታገልና ጥቅሟን ለማስጠበቅ ያስችላታል፡፡

**Proclamation No** … 2024

**A Proclamation to ratify the International Civil Aviation Convention Protocol to an Amendment to Article 50(A) and Article 56**

Whereas, Ethiopia is a signatory party to the Convention on International Civil Aviation opened for signature at Chicago on 7th day of December 1944;

Whereas, the Amendment to Article 50(A) and Article 56 of the Convention on International Civil Aviation is believed to be creating a conducive condition for the proper possibility of securing the national interest and the representation and admissibility worldwide;

Now, therefore, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

1/ **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Proclamation to ratify the Protocol relating to an Amendment to Article 50(a) and Article 56 of the Convention on International Civil Aviation No ………………2024"

2/ **Ratification of the PROTOCOL**

The Protocol relating to amendment to the Article 50(a) and Article 56 of the Convention on International Civil Aviation adopted on 6th of October 2016 during the 39th Session of the Assembly is hereby ratified.

3/ **Implementing organ**

The Ministry of Transport and Logistics in collaboration with other government organs is here by empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Amendment.

4/ **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this……day of the month of … /2024.

**Sahlework Zewde**

President of the Federal Democratic

Republic of Ethiopia